በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኖቬምበር 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከኖቬምበር 21-30 እና ከዲሴምበር 1-10 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2024
አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ - 1 -
ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ15 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች - 2 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 4 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 4 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ - 4 -
የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 4 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ- 6 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 - 6 -
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 6 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 7 -
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 21-30, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 9 -
ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 10 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 10 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 11 -



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

በኖቬምበር የሁለተኛዉ አሥር ቀናት ወደ ሀገራችን ሲገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ ከመጠናከሩ ጋር ተያይዞ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ ዝናብ በቦታና በመጠን ረገድ የተሻለ ነበር፡፡ እንዲሁም ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መጠናከር በማሣየታቸው ምክንያት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበራቸው የደመና ሽፋን በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላለ መጠን ያለዉ ዝናብ በመጨረሻዎች ቀናቶች ላይ ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ የደመና ክምችት የዝናቡ መጠንና ስርጭትም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ የተመዘገበ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎች ላይም ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው አከባቢዎች ለመጥቀስ ያህልም በአይራ 22.2፣ በአማን 32.5፣ በአንገር ጉትን 30.6፣ በአርጆ 26.6፣ በፉኚዶ 27.6፣ በጋምቤላ 31.3፣ በላሬ 50፣ በማሻ 30.1 እንዲሁም በቴፒ 22.2 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እምብዛም ያልተጠናከረ ቢሆንም፤ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በቢሾፍቱ 4.5፣ 2.0 እና 4.8፣ በአዲግራት 4.0፣ በሃሮማያ 3.8፣ 3.6፣ እና 4.2፣ በአለም ከተማ 4.8፣ 4.5 እና 3.4፣ በአምባ ማርያም 4.6፣ 3.4፣ 3.4፣ 4፣ 4.6፣ 4.6፣ 4.0፣ በአርሲ ሮቤ 4.5፣ 3.5፣ እና 4.5፣ በባቲ 4.6፣ በቡኢ 4.0፣ 4.6፣ 3.6፣ 3.6፣ 2.0፣ 2.6፣ 3.0፣ እና 4.6፣ በደባርቅ 5.0፣ በደብረ ብርሃን 4.0፣ 4.0፣ 4.6፣ -1.8፣ -0.2፣ 2.0፣ እና 4.8፣ በእነዋሪ 2.5፣ 2.4፣ እና 2.5፣ በጅግጅጋ 1.5፣ 1.0፣ ፣1.4፣ 3.6፣ እና 4.8፣ በማይጨዉ 4.5፣ በመሀል ሜዳ 4.2፣ 0፣ 0.6፣ እና 4.8. በሾላ ገበያ 2.0፣ 2.0፣ 2.1፣ 4.0፣ 4.1፣ 2.1፣ 2.0 እና 3.0፣ በወገል ጤና 4.8፣ 1.5፣ 2.0 እና 2.4፣ በወረኢሉ 4.2፣ እና 4.8 እንዲሁም በየትኖራ 4.8 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ16 የተለያዩ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ15 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የሀገሪቱ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 30.1 - 50.0 ሚ.ሜ የሚደርስ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል በአማን፣ በአርጆ፣ በላሬ፣ በነጆ እንዲሁም በቴፒ ይጠቀሳሉ (ምስል 1) ፡፡




ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ15 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፤ ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ የሸበል፣ የነጎብ፣ የቆራሂ እና የዶሎ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች ከ6-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-5 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን ባሌ፣ አርሲ፣ የኤረር፣ የጃረር ዞኖች ከ4-6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው:: በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከ11-80 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡

በሌላ በኩል የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ ባልሆኑት አከባቢዎች ማለትም በደቡብ ምስራቅና በመካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ የማሂ እና ሃሪ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀዲያ ዞን ላይ ከ2-5 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-3 ቀናት ያህል ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ የሸበል፣ የቆራሄ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሌ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ ደቡባዊ የሲዳማ ክልል ዞኖች ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡ በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የደቡብ ምስራቅ እና ምስራቅትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተስተውሏል። ይህም ሁኔታ በዚህ ጊዜ የመኸር ሰብል ስብሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን በሚያካሂዱ የሰሜን፣ የምስራቅ እና የመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አመቺ ሁኔታ ነበረዉ፡፡ በሌላ በኩል በጥቂት የምዕራብ አጋማሽ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበረው እርጥበት ነበራቸው። ይህም ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ዕድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች ተጨማሪ እርጥበት እንዲያገኙ ከማስቻል አንጻር ጠቀሜታ ነበረው። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተገኘዉ እርጥበት በበጋ ወቅት ለሚበቅሉ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በባሮ አኮቦ፣ በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በታችኛው አባይ ኪስ ቦታዎች እንዲሁም በታችኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለዉሃ ሀብት መጎልበት አውንታዊ ጎን ነበረው፡፡ በተቀሩት ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን፣ ተከዜ፣ የላይኛው ኦሞ ጊቤ፣ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝንበት ሳምንት ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ ምሥራቅ፣ መካከለኛው እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ይዘወተራል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ውርጭ የማስከተል ጥንካሬ ይኖረዋል። በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ፤ ደቡብ ምስራቅ እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በሚቀጥሉት ቀናት  በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀጣይነት ይኖራቸዋል (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋና ሰፊ ቦታዎችን የሚያካትት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ወላይታ፣ ኮንሶ፣ ጌዲኦ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፤ አሌ፣ አማሮ እና ቡርጂ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ከፋ፣ ቤንች ሸኮ፣ ዳዉሮ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበል፣ ኖጎብ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ፣ ጃረር እና ኤረር ፤ እንዲሁም ሀረሪ እና ድሬዳዋ ዞኖች ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪምወ ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ ባሉት አከባቢዎች ማለትም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ ቄሌም ወለጋ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር አኝዋክ እና ማዥንግ ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡

በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአማራ ክልል በሰሜን፣ ማዕከላዊና ደቡብ ጎንደር፤ ምስራቅ፤ ምዕራብ እና ሰሜን ጎጃም፤ አዊ ዞኖች እና ባህርዳር ዙሪያ፤ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፤ ሰሜን ሸዋ፣ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ፤ የደቡብና የደቡብ ምስራቅና ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ፋንቲ፤ ማሂ፣ ሃሪ፣ ቀልበቲ፣ ሃዉሲ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፤ አዲስ አበባ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ አሱማሌ ክልል የሲቲና እና ፋፋን ዞኖች፤ እንዲሁም ሀረሪ እና ድሬዳዋ ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 21-30, 2024 የሚኖረዉ
የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ የዲሴምበር የመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሰሜን፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛው እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ ባሉ ቀናት ውርጭ የማስከተል ጥንካሬ ይኖረዋል። በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ እና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በሚቀጥሉት የዲሴምብር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋና ሰፊ ቦታዎችን የሚያካትት ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፤ በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

Total Rainfall (mm) 1-10,Dec 2024




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10፣ 2024
የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት የሚኖረው እርጥበት በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ተዘርተው በእድገት ላይ ለሚገኙ እንደ ሽንብራ እና ጓያ ለመሳሰሉት የጥራጥሬ ሰብሎች እንዲሁም ለቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት እንዲኖራቸዉ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቦረናና ጉጂ ዞኖች ለተዘሩ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተጨማሪም ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃን



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በተለይም በሰሜን፣ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገሪቱ የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል አርሶ አደሮችም ሆኑ የሚመለከታቸው አካላት የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በባሮአኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በመካከለኛ እና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ተፋሰሶች ላይ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በታችኛው አባይ፣ በጥቂት መካከለኛው አዋሽ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ እንዲሁም አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ይኖራቸዋል። ይህ ሁኔታ የገፀ ምድር ውሃ ሀብትንና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አውንታዊ ሚና ይኖረዋል። በተለይም እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀውን እርጥበት የውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አኳያ የጎላ ጠቀሜታ ይኖራዋል። በአንጻሩ የተከዜ፣ የአዋሽ፣ የአይሻ እና የመረብ ጋሽ ተፋሰሶች በደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et